# አመክንዮና ስሜት

አመክንዮ (logic) እና ስሜት (emotion) ሁለቱም በፖለቲካ ውስጥ የራሳቸው ሚና አላቸው። በአፍሪካ ውስጥ ብዙ ሰው ስሜታዊ ይሆናል ምክንያቱም ሥራ አጥነትና የዋጋ ግሽበት የመሳሰሉት ችግሮች ሕዝብን ያማርራሉ። ማህበራዊ ጥያቄዎች መልስ ባላገኙበት ሠዓት ስሜታዊነት ብቻ ነው እውስጥ የታመቀን ብሶት ማስተንፈሻ።

ስሜት ብዙሃኑን ማንቀሳቀሻ (manipulation) ሞተር ነች። ስሜት በሰው ልጅ ጠባይና ባህርይ ውስጥ የመሸገች በመሆኗ በማስተባበርም ይሁን በመበታተን ወይም በሌሎች ማህበራዊ ጉዳዮች ውስጥ የማይናቅ አስተዋጾ ታደርጋለች። ፖለቲካ በስሜት አትበጅም ግን አነሰም በዛም ቁርኝት (interaction) አላቸው።

አመክንዮ አሳማኝ ሃሳብ፣ ምክንያት፣ ህግ፣ ንፅፅር - ሊሆን ይቻላል። በእርግጥ እነዚህ ቃላት ብቻቸውን አመክንዮን በሚገባ ይገልጻሉ ሊባል አይችልም። አመክንዮ እውነትን መፈለግ ማለት ነው። ሥነ-አመክንዮ ደግሞ "ትክክለኛ የሆነውን ምክንያት ለማገኘት የሚደረግ ጥናት ነው" ቢባል "ጽንሱን በተሻለ ለመረዳት ይጠቅም ይሆናል። ፈላስፎች "ሥነ-አመክንዮ የሥነ-ልቦና ትምህርት አይደለም" ይላሉ። "ይልቁንም ቀደምት የሆነው አመክንዮ - ምክንያትን አፈላለግን -የሚያስተምረን ነው" ሲሉ ሃሳብ ያክላሉ። "ምክንያታዊ መሆን ከእድሜ መግፋት ጋር አብሮ ይሄዳል፣ አመክንዮ ግን የእድሜ ገደብ የለውም" የሚል ጥናታዊ ጽሑፍም በስፋት ይገኛል።

ምክንያታዊ ለመሆን በተገቢው መንገድ ማሰብ ያስፈልጋል። አንድ ውሳኔ ላይ ለመድረስ እውነትን መረዳት ጠቀሜታ አለው። እስኪ ከዚህ በታች ያለውን
አመክንዮ (logic) እንመልከት።

ምሳሌ 1 - ሃቀኛ የሃገር መሪ ሙስናን ይጠየፋል፤
እገሌ -ሃቀኛ የሃገር መሪ ናቸው፣
ስለዚህ፤ እገሌ ሙስናን ይጠየፋሉ።

ምሳሌ 2 - የኃይማኖት አባቶች በንዋይ አይጠመዱም፣
አባ --- የኃይማኖት አባት ናቸው፣
ስለዚህ፤ አባ --- በንዋይ አይጠመዱም።

አመክንዮ ትክክለኛውንና ተገቢውን ሃሳብ መከተል ማለት ነው። ከላይ በሁለቱ ምሳሌዎች ላይ እንደተመለከትነው የመጀመርያዎቹ ዓረፍተ ሃሳቦች በተቻለ መንገድ ትክክለኛ መሆን አለባቸው። ሃቀኛ የሃገር መሪ ሙስናን መጸየፉ ትክክል ነው። የኃይማኖት አባቶች በንዋይ አለመጠመዳቸውም ትክክል ነው። ከዚህ ውጭ ያለው

ስህተት ነው። የሃገር መሪውን ሙስናን ስለሚጸየፉ ነው የምንወዳቸው። አባ ለሁላችን ምሳሌ የሆኑ፣ አፍቅሮ ነዋይ የማይታባቸው አባት ስለሆኑ ነው የምንከተላቸው። የሃገር መሪውም አባም፣ ሁለቱም፣ ጥሩ ባህርያትን ካላዘሉ አንከተላቸውም። መጥፎ ባህርይ እየታየባቸው ከተከተልናቸው ግን በስሜት ተነድተን ወይም በጥቅም ተይዘን ሊሆን ይችላል። ስሜት አይላ አመክንዮ ከታቀበች ወደ ትክክለኛው ግንዛቤና የመጨረሻ ግብ መድረስ አይቻልም።

ግፍና በደሉ ሲያይል በተለይ ደግሞ የፖለቲካ ፓርቲዎቹ አቅም ውሱን ሲሆን ጋዜጠኞችና አርቲስቶች የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን ይታገላሉ። ዜማና ግጥም ሰዎችን ለትግል ያነሳሳሉ። ኪነ ጥበብ አምባገነኑን ሥርዓት መታገያ ትሆናለች። ወጣቶች ብርቱውን አርቲስትና ጠንካራውን የሰብዓዊ ተሟጋች ይከተሉታል። የሚገርመው በዝባዦችም ይህን ያደርጋሉ። እነሱም እንዲወደሱ አልያም ድጋፍ እንዲያገኙ ታዋቂ ግለሰቦችን ቢቻል በገንዘባቸውም ይገዛሉ ካልሆነም በሥልጣናቸው ይስፈራሩሉ።

ጨቋኞች ከያኔዎችን፣ አርቲስቶችንና የሠብዓዊ መብት ተሟጋቾችን የሚይዙት ዕቅዳቸውን ለመተግበር፣ ዓላማቸውን ከግብ ለማድረስ ሊሆን ይችላል። በዝባዦች በገንዘባቸው ሁኔታን መቆጣጠር ይችሉበታል። ይህ ደግሞ ያደጉበት ሥልት ነው። ሊጂክ መከተሉ፣ ምክንያታዊ መሆንና ዞር ብሎ ማሰቡ ደግሞ የኪነ ጥበብ ባለሙያዎቹ ድርሻ ነው። እውነትን ካልተረዳን ሃቅን ካልፈተሽን የተሳሳተ ውሳኔ ላይ መድረስ ብቻ ሳይሆን ተከታዮቻችንንም እናሳስታለን። እንደነ እስክንድር ነጋ ያሉ ጋዜጠኞችና እንደነ ቴዲ አፍሮ ያሉ ከያኔውች፣ ጥቅማጥቅም በሳህን ሳይቀርብላቸው ቀርቶ አይደለም እዚህ የደረሱት የሕዝብን ጥቅም ስላስቀደሙ እንጂ።

የዚህ ጽሑፍ ዋና ዓላማ ስለ አመክንዮ ለማስተማር ሳይሆን ብዙውን ጊዜ ለምን ከአመክንዮ ይልቅ ስሜት ትበረታለች የሚለውን በትንሹ ለማየት ነው።

ፖለቲከኞች በምርጫ ወቅት "ይህን አደርግላችኋለሁ - ምረጡኝ" ይላሉ። ብዙ ሰዎች - ያ- ቃል የተገባለቸው ነገር የሚፈጸምላቸው እየመሰላቸው ተናጋሪውን እጩ ይመርጣሉ። ከዓመታት በኃላም ይኸው ይደገማል፣ ጠብ የሚል ግን የለም። ለዚህ ነው ሰዎች ከፖለቲከኞች ይልቅ ከያኔዎችን፣ አርቲስቶችንና የሠብዓዊ መብት ተሟጓቾችን ለመከተል የሚገደዱት። ከያኔው፣ አርቲስቱና የሠብዓዊ መብት ተሟጋቹ - ቢያንስ ቢያንስ – ብልሹ ፖለቲካውን ስለሚያብጠለጥሉ፣ ገዥዎችን መላወሻ ስለሚያሳጡና ሙሰኛውን አደብ ስለሚያሲዙት የደጋፊዎቻቸውን ስሜት ያረካሉ።

ስሜት ብቻዋን ግን ለፖለቲካ ድርጅቶት መጎልበት መልካም አይደለችም። ብዙሃን በስሜት ከተነዱ ዘላቂ መፍትሄ የሚያመጣላቸውን ትልቅ
ተቋም (institution)መመስረት የማይችሉበት ደረጃ ላይ ይደረሳሉ። ምሁራን በሰበብ አስባብ ከተገፉ፣ መድረክ ከተነፈጉ ጠብ የሚል ነገር አይመጣም፣ ችግሩ ይባባሳል

እንጂ። ጠንካራ ተቋም በሌለበት ግለሰቦች መድረኩን በግላቸው ሲቆጣጠሩት ወደ ዴሞክራሲ የሚደረገው ሂደት ይዘገያል። ጭብጨባ ሲበዛ እውቀት ትደበቃለች፣ አመክንዮም ግራ ይገባታል። በስብሰባ ላይ አብዛኛውን ለማሳመን ወይም ለማስተማር ስሜትን ማርገብ መቻልና ሳይዋሹ ሃቁን መግለጽ ነው አዋቂነት። የመጣው ይምጣ ብሎ እውነቱን የሚናገር ነው የሕዝብ ወገን። ከዚህ ውጭ መድረክ ላይ መቆም አግባብ አይደለም።

ተከታዮች ይኑሯቸው እንጂ በምኑም ምኑም መድረኩ ላይ የቆሙ ግለሰቦች ብቻቸውን ተቋም አይደሉም። ጠንካራ የፖለቲካ ተቋም በአመክንዮ የሚመራ -የፖለቲካ ፓርቲ - ነው። ይህ የፖለቲካ ፓርቲ ትክክለኛ መርህን በመምረጥ ምክንያታዊ ለመሆን ዘወትር መጣርና መማር አለበት። አሁን ላይ ጠንካራ ፓርቲ ሊኖር የቻለ አይመስልም። እንደውም የደርጉ ዘመን ኢሕአፓና መኢሶን ሳይሻሉ አልቀሩም። ጠንካራ ፓርቲ እንዳይኖር አቶ መለስ በርካታ ድብቅ ሴራዎችን ፈጽመዋል። በሃያ ሰባቱ ዓመታት የሙስናና የሌብነት ሥርዓት በርካታ ታጋዮች ዘግናኝ ግፍ ተፈጽሞባቸዋል። ጨካኙ ወያኔ በርካቶችን አሰድዷል፣አፍኗል፣ አካለ ጎዶሎ አድርጓል፣ ጥፍር ነቅሏል፣ አኮላሽቷል፣ በባለጌዎች አስደፍሯል። ይህን የሠማይ ስባሪ የሚያህል መከራና ስቃይ ተቋቁመው ለዛሬ ያደረሱን ጀግኖች ክብር ይገባቸዋል።

ተንኮልን ሻጥር ገና አልተቀበሩም። ተንኮልና ሻጥር እንዲቀበሩ አዋቂዎች ስብዕናን ከማሽሞንሞን ይልቅ ጥልቅ ሃሳብ (critical thinking) መፈንጠቅ አለባቸው። የተቋምን መሠረት ማነጽ እንደመቃወም ቀላል አይደለም። ሃሳብ በእውቀትና ምርምር እንጂ በስሜት አትገኝም። ፖለቲካ መልካም የምትሆነው - ፖለቲከኞች የማያስማሙ አመክንዮአዊ ያልሆኑ ስህተቶችን ነቅሰው አውጥተው መግባባት ላይ መድረስ ሲችሉ ነው። አንዳንድ ጊዜ ሰዎች የማይግባቡት በቂ ምክንያት ኖሯቸው ላይሆን ይልቁንም አመክንዮን ባለመቀበል ሊሆን ይችላል። እነሆ ታድያ ግራና ቀኙ ተከራካሪ ወገን አሳማኝ ማስረጃ ሲያጣ ደጋፊ ለማግኘት ብቻ ነገሮችን በግምት(opinion) ያስቀምጣል። ግምት ደግሞ ቤቱን ስትቆጣጠር ስሜታዊነት ትነግሳለች።

የዳበረ የፖለቲካ ባህል እንዲሰፍን፣ ስሜታዊነት ጋብ ማለት አለባት። ጠንካራ የፖለቲካ ፓርቲ እንዲኖር አመክንዮ ማደግ አለበት። የፖለቲካ ፓርቲ በአዋቂዎች፣ ምሁራንና ጉጉት በማይበረታበቸው የሕዝብ አጋሮች ሲመራና ሃሳብ መሬት ስትወርድ ከድህነት ወለል በታች ያሉ ጭቁኖች በቀን ሶስቴ ይበላሉ፣ ልብስና መጠለያም ይኖራቸዋል። ስሜታዊነት ጋብ ስትል አለማቀፉን ሻጥር መቆጣጠር ይቻላል። የሃገራችን አቀማመጧ የኃያላን አገሮችንና የአረቦቹን ትኩረት ይስባል። ተንክል አዘሉ ስልታቸው የሚገደበው በስሜት ሳይሆን በጥበብ ነው። ጥበብ ወደ ኋላ ተመልሳ አክሱም ላሊበላን የገባንበትን እውቀት ካልመልሰችልን፣ አራሹን ከኋላ ቀር አስተራረስ ካላላቀቀችው፣ በድህነት

የሚሰቃየውን የገጠሩን ሕዝብ መሠረታዊ ችግር ካልቀረፈችለት ነገር ሁሉ — ውሃ ቢወቅጡት እንቦጭ - ይሆናል።

የኢሕአዴጉ ግፈኛ የኪራይ ሰብሳቢነትና የሙስና ሥርዓት መታቀብ ለሃሳብ መንሸራሸር ምቹ ሁኔታ የፈጠረ ይመስላል። ይህን እድል በብስለት መጠቀም ደግሞ የሕዝብ ጉዳይ ነው። ሕዝብ ደማቅ ንግግሮችን ብቻ መከተል የለበትም። ሕዝብ የኔ፣ ለኔ የሚለው ከድህነትና እርዛት፣ ከሥራ አጥነትና ስደት፣ ከዘር ጥቃትና አድሎ፣ ከምዕራብያውኑ የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝና ዓለም ዓቀፉ የፋይናንስ ተቋማት ሤራ፣ ወዘተ፣ የሚከልለው በሳል የፖለቲካ ፓርቲ እንዲመሰረት በጽኑ መታገል አለበት። ሰዎች የግለሰቦችን አምልኮ (cult) አቁመው ምሁራን ደግሞ ባዶ ተስፋ ሰጪ ድብቅ ቋንቋ (jargon) መጠቀም አቁመው የጠንካራ ፖለቲካ ፓርቲ ጎልውና ግንባታ ላይ መረባረብ አለባቸው።

የኪነ ጥበብ ሰዎች በሙያቸው ምክንያታዊነትን የሚያግዙ ሥራዎችን ሲከውኑ የፖለቲካ ፓርቲዎችና አባላቶቻቸው በእውቀትና ጥበብ ይመነደጋሉ። በየዓመቱ በየዘመን ሽግግሩ በርካታ (wish) ምኞቶች ተደርገዋል። ምኞቶቹ ግን የሕልም እንጀራ (wishful) ሆነው ቀርተዋል። ዛሬም ጳጉሜ የሠላም ቀን፣ የፍቅር ቀን፣ የይቅርታ ቀን፣ የመደመር ቀን፣ የአንድነት ቀን ተብላለች። ከዓመት ዓመት ሽግግሩ ምኞት ብቻ ሆነው እንዳይቀሩ ሃገር ወደ ዲሞክራሲ እንድትሸጋገርና፣ ብልጽግና እንዲመጣ፣ የድሆች ኑሮ እንዲያብብ ኪነ ጥበብ ሕዝቡ እንዲደራጅና እንዲማር የማያቋርጥ ቅስቀሳ ማድረግ ይጠበቅባታል። ኪነ ጥበብ በየቦታው መረጋጋት እንዲሰፍን መታገል አለባት። የስሜት ቴርሞሜትር እያሽቆለቆለ የአመክንዮው ደግሞ ወደ ላይ ከፍ ሊል ይገባል።

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር